ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

# የተቀናጀ የተፈጥሮ ሀብት አያያዝና አጠቃቀም
## የሞዴል ተፋሰስ ትግበራ ማዕቀፍ ሰነድ



መጋቢት 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


1. መግቢያ ........ 1
2. የቅንጅታዊ አሠራር አስፈላጊነት ........ 2
3. የቅንጅታዊ አሰራሩ ግብ እና ዓላማዎች ........ 2
3.1. ግብ ........ 2
3.2. ዓላማ ........ 2
3.3. ዝርዝር ዓላማዎች ........ 3
4. የቅንጅታዊ አሠራር የለውጥ ፅንሰ-ሐሳብ ........ 4
5. የአተገባበር ሥርዓትና ስልት ........ 5
6. የትግበራ ወሰንና ጊዜ ........ 5
7. የተመረጡ የትግበራ ተፋሰሶች ........ 6
7.1. የተፋሰሶች ምልመላ መሥፈርት ........ 6
7.2. ለሙከራው የተመረጡ ተፋሰሶች ........ 6
8. የውጤት አመልካቾች ........ 7
9. የአቅም ግንባታ ሥራ ........ 10
9.1. የሰው ኃይል አቅም ግንባታ ........ 10
9.2. የቁሳቁስ አቅም ........ 10
10. የባለድርሻ አካላት ልየታና ሚና ........ 10
11. ዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ........ 11
11.1. የዕቅድ ዝግጅት ........ 11
11.2. የድጋፍ፣ የክትትልና የሪፖርት ሥርዓት ........ 11
11.3. የምርምርና ሥርፀት መድረክ ........ 12
11.4. ምርጥ ተሞክሮ የማስፋት ሥራ ........ 12
12. ስጋቶች እና የመፍትሔ ርምጃዎች ........ 12
13. የሚያስፈልግ በጀት ........ 13
13.1. የሙከራ ሥራ በጀት ........ 13
13.2. የማስፋት ዘመን በጀት ........ 13
ዋቢ/ማጣቀሻ ........ 14

# የሠንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ 1፡ የቅንጅታዊ አሠራር የለውጥ ጽንሰ-ሃሳብ .......... 4
ሠንጠረዥ 2፡ የተመረጡ ተፋሰሶች ዝርዝር .......... 6
ሠንጠረዥ 3፡ በተፋሰሱ የሚተገበሩ የቅንጅታዊ ሥራ ተግባራትና የውጤት አመልካቾች .......... 7
ሠንጠረዥ 4፡ የባለድርሻ አካላት ሚና .......... 10
ሠንጠረዥ 5፡ ስጋቶችና የመፍትሔ ርምጃዎች .......... 12
ሠንጠረዥ 6፡ የቅንጅታዊ ሥራዎች የሦስት ዓመት የሙከራ ጊዜ ሠሌዳ .......... 13

# 1. መግቢያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ ለግብርናው ዘርፍ ምቹ የሆነ የተለያየ ስነ-ምኅዳር ቀጠና፣ የአፈር ዓይነት፣ የከርሰ-ምድርና ገጸ-ምድር የውሃ ሀብት የታደለች ሀገር ናት፡፡ አጠቃላይ ከ1.1 ሚሊዮን ስኩየር ኪሎ ሜትር በላይ የቆዳ ስፋት እና 110 ሚሊዮን የሚገመት የህዝብ ቁጥር ያላት ስትሆን ከዚህ ውስጥ 79 በመቶ የሚጠጉ የገጠር ነዋሪዎችን ያቀፈ ነው፡፡ የገጠሩ ማህበረሰብ በድህነት ተጋላጭነቱ አሁንም ከፍተኛ ሲሆን፣ በተለይም ኑሮአቸው በዝናብ ጥገኝነት ላይ የተመሠረተ አርሶ አደሮች ላይ ችግሩ የጎላ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ዓመታዊ የመሬት መራቆት ወጪ ከ2-3 በመቶ የሚሆነውን የግብርና አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርትን (GDP) የሚሸፍን ከመሆኑም ባሻገር ለታችኛው ተፋሰስ የጎርፍና የደለል አደጋ የመጨመር ሥጋት እየፈጠረ ይገኛል፤ የአፈር ለምነት እና የግብርና ምርትን በመቀነስ የመሬት መራቆትንና የኑሮ ደህንነትን በመጉዳት ላይ ነው፡፡ በመሆኑም የተቀናጀ ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት አያያዝና አጠቃቀም ልምዶች እና አካሄዶች በማስፋት እና የተራቆቱ ተፋሰሶችን ወደ ነበሩበት በመመለስ የተፈጥሮ የመቋቋም አቅምን መገንባት፣ የአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተፅዕኖን መቀነስ እና የማኅበረሰቡን የኑሮ ደረጃ ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡

ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም የግብርና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባሻገር የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነትን ለመቋቋም፣ አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባትና የገጠር ስራ ዕድል ለመፍጠር እንዲሁም አጠቃላይ ኢኮኖሚውን ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ለሚደረገው መዋቅራዊ ሽግግር ጉልህ አስተዋጽዖ ያደርጋል፡፡ በሀገራችን በመደበኛና በሕዝብ ተሳትፎ ከሚተገበሩ ሥራዎች በተጨማሪ ከልማት አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር በርካታ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ፕሮገራሞችንና ፕሮጅክቶችን በተለያዩ ክልሎች በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ ከእነዚህም ለመጥቀስ ያህል ዘላቂ የመሬት አያያዝ ፕሮገራም (sustainable land management Programme)፣ በአየር ንብረት አፈፃፀም የመሬት አያያዝ (Climate Action through Land Management Project)፣ ተሳትፎአዊ አነስተኛ መስኖ ልማት ፕሮጀክት (Participatory Small-scale Irrigation Development Project) ወዘተ. ይገኙበታል፡፡

ይሁን እንጂ እስካሁን የተለያዩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ሲቀረፁም ሆነ ሲተገበሩ እርስ በርስ እንዲቀናጁና የተፋሰሱን ችግሮችና ያለውን ፀጋ ታሳቢ ባደረገ መልኩ በዓላማ እንዲደጋገፉ ባለመደረጋቸው ምክንያት የሥራ ድግግሞሽ በማስከተሉ የሚፈለገውን ውጤት ማስገኘት አልቻለም፡፡ ከዚህም ባሻገር በመንግሥት ፕሮግራሞችና በህዝብ ተሳትፎ የወጣው ከፍተኛ ጊዜ፣ ጉልበትና መዋዕለ-ንዋይ ያለአግባብ መባከኑን የተደረጉ ጥናቶችና ሪፖርቶች ያሳያሉ፡፡

ስለሆነም በተፈጥሮ ሀብት ዘርፍ ውስጥ የሚገኙ ፕሮግራሞችን/ፕሮጀክቶችን፣ መደበኛ የሥራ ክፍሎች እንዲሁም አጋር አካላትን አቀናጅቶ በመምራት፣ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችንና አሠራሮችን በአግባቡ በመጠቀም የተፈጥሮ ሀብታችንን በዘላቂነት ለማልማትና ለመጠቀም ብሎም ዘላቂ የግብርና ዕድገት ለማምጣት የሚያስችል ቅንጅታዊ አሠራር ለመዘርጋት ይህ ሠነድ ተዘጋጅቷል፡፡

ይህ የቅንጅታዊ አሠራር ሰነድ ሞዴል ተፋሰሶችን መሰረት ያደረገ የተፈጥሮ ሀብትን በዘላቂነት በማልማት የአርሶ አደሩን ኑሮ ለማሻሻልና ለማጎልበት የሚያስችሉ የተቀናጁ ተግባራትን ለማስፋፋት ያግዛል፡፡ በሂደትም የተገኘዉን ተሞክሮ በመቀመር ከሌሎች ዘርፎች፣ ተጠሪ ተቋማት እንዲሁም ከሌሎች አካላት ጋር ተቀናጅቶ በመሥራት የግብርና ሴክቴሩ የሚጠበቅበትን አገራዊ ተለክዕኮ እንዲወጣ የማስቻል የቅንጅታዊ ሥራ ለመሥራት ግብአት ለመስጠት ነው፡፡

# 2. የቅንጅታዊ አሠራር አስፈላጊነት

ይህንን ሰነድ ማዘጋጀት ያስፈለገበት ዋና ምክንያት እስካሁን በነበረው የተፋሰስ ልማት ዕቅድ፣ ትግበራና አፈጻጸም ሂደት በፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች እና በመደበኛ በሚሠራዉ ሥራ መካከል የነበረውን ያልተቀናጀ አሠራር ክፍተት በማሻሻል የተፈጥሮ ሀብት ልማት አፈጻጸም ወደ ላቀ ደረጃ ማሳደግ የሚያስችል አሰራር ለመዘርጋትና የአካባቢውን መልክዓ-ምድር ገጽታ እንዲሻሻል በማድረግ የህብረተሰቡን የኢኮኖሚ ተጠቀሚነት እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው፡፡

በዚህ ሠነድ ላይ የተቀመጠውን የአሰራር ስርዓት ጥቅም ላይ በማዋል የሥራ ድግግሞሽን በማስቀረት የሀብትና የጊዜ ብክነትን መቀነስ፣ የክትትልና ድጋፍ ውስንነትን መቅረፍ፣ ወጥነት የጎደለውን የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ክፍተትን ማሻሻል፣ የተሻሻለና ዘመናዊ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አስተዳደር እንዲሁም የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ስርዓትን በመዘርጋት፣ የመፈጸም አቅምን ማሳደግና የህብረተሰቡን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ ሁሉንም ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች እና ባለድረሻ አካላት የተሻለና የተቀራረበ አፈጻጸም እንዲኖራቸው በፉክክር ሳይሆን በትብብር መንፈስ ተቀናጅተውና ተደጋግፈው እንዲሠሩ ማስቻል እንዲሁም በመካከላቸው የክህሎትና ዕውቀት ሽግግር ለመፍጠር ነው፡፡

# 3. የቅንጅታዊ አሰራሩ ግብ እና ዓላማዎች

## 3.1. ግብ

ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ በማጎልበት የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ የመቋቋም አቅም ለመገንባት፣ የግብርና ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ፣ የምግብና ስርዓት-ምግብ ዋስትና በዘላቂነት ለማረጋገጥ እና የህብረተሰብን ኑሮ ለማሻሻል ጉልህ አስተዋጽኦ ማበርከት ነው፡፡

## 3.2. ዓላማ

የዚህ ሰነድ ዐቢይ ዓላማ ቀልጣፋና ውጤታማ ቅንጅታዊ አሠራር በመዘርጋት የሥራ ድግግሞሽንና የሀብት ብክነትን መቀነስ ብሎም ተፋሰስን መሠረት ያደረገ የተፈጥሮ ሀብት አያያዝና አጠቃቀም ዘላቂነትን ማረጋገጥ ነው፡፡

## 3.3. ዝርዝር ዓላማዎች

- ነባር ሞዴል ተፋሰሶችን በመምረጥ የተቀናጀ የተፈጥሮ ሀብት ሥራዎችን ማጠናከር፤
- የተፋሰስ ልማት ተጠቃሚዎችን የኑሮ ደረጃ በዘላቂነት ማሻሻል፤
- የአየር ለውጥ ተጽዕኖን የመላመድና የመቋቋም አቅምን መገንባት፤
- ለተቀናጀ የተፈጥሮ ሀብት ልማት አስቻይ ሁኔታዎችን መፍጠር፤
- በቅንጅታዊ አሠራር የተገኙ ውጤቶችን፣ ምርጥ ተሞክሮዎችንና ልምዶችን በመቀመር ወደ ሌሎች ተፋሰሶች ማስፋት፤

## 4. የቅንጅታዊ አሠራር የለውጥ ፅንሰ-ሐሳብ

ሠንጠረዥ 1፡ የቅንጅታዊ አሠራር የለውጥ ጽንሰ-ሃሳብ

| ተ.ቁ | ቁልፍ ችግሮች (Key Challenges) | የረጅም ጊዜ ግብ (Impact) | የመካከለኛ ውጤት (Outcome) | የአጭር ጊዜ ውጤት (Output) | ተግባራት (Interventions) |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በዘርፉ የሚዘጋጁ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተናብቦ ያለመተግበር | • በተቀናጀና በተናበበ ፖሊሲና ስትራቴጂ መሠረት የተፈጠረ ምቹ ሁኔታ | • በዘርፉ የተሻሻለ ቅንጅታዊ አሠራር | • የተናበበ የፖለሲና ስትራቴጂ ሠነዶች | • የማይናበቡ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን መለየት<br>• በተለዩ ክፍተቶች ላይ የምክክር መድረክ ማዘጋጀት<br>• በምክክር መድረኩ በተገኙ ውጤቶች መሠረት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንዲናበቡ ማድረግ |
| 2 | ተመሣሣይ ኃላፊነትና ድርሻ ያላቸው ተቋማትና የሥራ ክፍሎች ተናብቦ ያለመፈፀም | • የተፈጠረ ምቹ የአሠራር ሥርዓት | • የተሻሻለ የጋራ ዕቅድና የአሠራር ሥርዓት | • የተለዩ ተመሣሣይ ሥራ ያላቸው ተቋማትና የሥራ ክፍሎች<br>• የተካሄደ የጋራ ዳሰሳ ጥናቶች<br>• የተናበበ የጋራ የዕቅድ ሠነድ<br>• የተካሄደ የጋራ ሥልጠና<br>• የተዘረጋ የመረጃ ሥርዓት<br>• የጋራ ግብአት አቅርቦት<br>• የተዘረጋ የተቀናጀ የጋራ የክትትልና የድጋፍ ሥርዓት | • ተመሣሣይ ኃላፊነትና ድርሻ ያላቸው ተቋማትና የሥራ ክፍሎችና ተግባራትን መለየት<br>• የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ<br>• የጋራ ዕቅድ ማዘጋጀት<br>• የተቀናጀ ሥልጠና መስጠት<br>• የተቀናጀ መረጃ ሥርዓት መዘርጋት<br>• ግብአቶችን በሚፈለገው አግባብ ማቅረብ<br>• የጋራ ክትትልና ድጋፍ አሠራር መዘርጋት |
| 3 | የፕሮጀክቶችና ፕሮገራሞች የሥራ ድግግሞሽ | • በፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች መካከል የቀረ የስራ ድግግሞሽ | • የተዘረጋ የስራ ድግግሞሽን የሚያስቀር የአሠራር ሥርዓት | • የተለዩ ተመሳሳይ ተግባራት ያላቸው ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች ፣<br>• የጋራ ዕቅድ፣ ክትትልና ድጋፍ የዘረጉና የተገበሩ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች | • የፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች በተመሣሣይ ቦታ ተመሣሣይ ተግባራት መለየት<br>• የተለዩንት ተግባራት እንደየፕሮጀክቶች የሥራ ባህርይ ከፋፍሎ መተግበር<br>• በተለዩት ተግበራት መሠረት አንደኛውን የማይሠራውን ተግባር ሌላኛው እንዲሸፍን ማድረግ<br>• በፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች መካከል የጋራ ዕቅድ፣ ክትትልና ድጋፍ አሠራር መዘርጋት |
| 4 | የሀብት ብክነት | • የቀነሰ የሀብት ብክነት | • በቅንጅት ጥቅም ላይ የዋሉ ሀብቶች | • የተለየ ብክንነት የሚደርስበት ሀብት<br>• የሀብት ብክነት ለመቀነስ የተለየ አሠራር | • ያሉትን ሀብቶች መለየት<br>• የሀብት ብክነት የሚታዩባቸው አሠራሮችን መለየት<br>• ያሉትን ሀብቶች ማቀናጀት |
| 5 | የመረጃ ሥርዓት ክፍተት | • የተፈጠረ የመረጃ ቅብብሎሽ | • የተሻሻለ የመረጃ ቅብብሎሽ | • የተዘረጋ የመረጃ ሥርዓት | • የመረጃ ሥርዓት መዘርጋት |

## 5. የአተገባበር ሥርዓትና ስልት

ቅንጅታዊ አሰራሩን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የሚከተሉት የአተገባበር ስልቶችና የአሰራር ሥርዓቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

- ለዚህ የሙከራ ትግበራ በዘርፉ ሥር ያሉ የሥራ ክፍሎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ያላቸውን የሰው ኃይል፣ የገንዘብና ቁሳቁስ ሀብት እንዲያቀናጁ ይደረጋል፡፡ ሥራውን የሚስተባብር የሰው ኃይል በሚኒስትር ዴዔታው ጽ/ቤት ሥር ይደራጃል፡፡ የሙከራ ጊዜ ቅንጅታዊ አሠራር በተሠጠው አቅጣጫ መሠረት ዘላቂ መሬት አያያዝ ፕሮግራም በጊዜአዊነት የሚያስተባብረዉ ሲሆን የጥናት ሥራዎች እንደተጠናቀቁ ለቅንጅታዊ ሥራው አንድ አስተባባሪና አንድ የክትትልና ግምገማ ባለሙዎች እንዲመደቡ ይደረጋል፡፡
- ሞዴል ተፋሰሶቹ በሚገኙባቸው ክልሎችና ወረዳዎች ቅንጅታዊ ሥራውን የሚያስተባብር ፎካል የሚመደብ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የባለሙያ ቡድን ይደራጃል፡፡
- በተመረጡ ተፋሰሶች የእቅድ ዝግጅትና ትግበራ በግብርና ሚኒስቴር በተዘጋጀው እና በተከለሰው የማኀበርሰብ አቀፍ አሳታፊ የተፋሰስ ልማት አተገባበር መመሪያ ሠነድ (MoA, 2020) መሠረት ይሆናል፡፡
- የሙከራ ትግበራው በሚካሄድባቸው ተፋሰሶች ላይ የሚተገበሩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ተለይተው እንደየሥራቸው ባህሪይ በተፋሰስ ውስጥ ሊሠሯቸው የሚችሉ ሥራዎች፣ በተመረጡት ተፋሰሶች ያሉ ችግሮችና ጸጋዎች እንዲሁም የማኀበረሰብ ተቋማት ያሉበት ሁኔታ ይለያሉ፡፡ በየተፋሰሱ የሚተገበሩ ሥራዎች በተፋሰሱ ውስጥ እየሠሩ በሚገኙ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች ባላቸው የአሠራር ሥርኣት መሠረት ይሆናል፡፡ የተገኘውን የጥናት ውጤት እና የተቀናጀ የማኀበረሰብ ተፋሰስ ልማት መመሪያን መሠረት በማድረግ ዝርዝር የማስፈፀሚያ ዕቅድ ይዘጋጃል፡፡
- በተፋሰሱ ውስጥ በሚሠሩ ፕሮግራሞችና/ፕሮጀክቶች እና በሌሎች አጋር አካላት ለማይሸፈኑ ተፋሰሶችና ሥራዎች በተለየ መንገድ ማስፈፀሚያ ሀብት በማፈላለግ እንዲተገበሩ ይደረጋል፡፡

## 6. የትግበራ ወሰንና ጊዜ

የቅንጅታዊ አሠራር የሙከራ ትግበራው ከአምስት ክልሎች (አማራ፣ አፋር፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ፣ ሲዳማ) በተመረጡ አሥር የሙከራ ተፋሰሶች ላይ የሚከናወን ይሆናል (ሠንጠረዥ-2)፡፡ የቅንጅታዊ አሠራር ሙከራው የሚመራውም በተቀናጀ የተፋሰስ ልማት መመሪያ መሠረት ሲሆን ከዚህ ሙከራ የሚገኘውን ልምድና ተሞክሮ በመቀመር ወደ ሌሎች የሀገሪቱ ተፋሰሶች የማስፋት ሥራ በቀጣይ ይሠራል፡፡

የሙከራ ትግበራው በዋንኛነት ትኩረት የሚያደርገው በተፈጥሮ ሀብት ዘርፍ ያሉት የሥራ ክፍሎች የሚያካሄዱቸው የመደበኛና የፕሮጀክት ተግባራትን ከዕቅድ ዝግጅት ጀምሮ በበጀትና በሰው ኃይል እንዲሁም በክትትልና ድጋፍ እንዲቀናጁ በማድረግ ይሆናል፡፡

የሙከራ ሥራው የዝግጅትና ትግበራ ጊዜ አራት ዓመት (2015 እስከ 2018 ዓ/ም) ሲሆን የማስፋት ጊዜው ደግሞ አምስት ዓመት (2019 እስከ 2023 ዓ/ም) እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡

# 7. የተመረጡ የትግበራ ተፋሰሶች

## 7.1. የተፋሰሶች ምልመላ መሥፈርት

በሀገሪቱ በርካታ የማህበረሰብ ተፋሰሶች ያሉ ቢሆንም ለቅንጅታዊ የሙከራ ትግበራ የሚመረጡ ተፈሰሶችን ለመምረጥ የሚከተሉትን መስፈርቶች በመጠቀም ይሆናል፡፡

- የተለያዩ ነባር እና የተቀናጁ ስራዎች በተፋሰሱ ዉስጥ መኖር፤
- ጅምር የተቀናጀ የአሰራር ስርዓት መኖር፤
- በተፋሰሱ ውስጥ እየሠሩ ያሉ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች በብዛት መኖር፤
- የወረዳው የመፈፀም አቅምና የአመራር ቁርጠኝነት፤
- ለተጨማሪ የፋይናንስ እድገት ያለው እምቅ አቅም፤
- ተፋሰሱ ለድጋፍና ለክትትል ያለዉ አመቺነት፤

## 7.2. ለሙከራው የተመረጡ ተፋሰሶች

*ሠንጠረዥ 2፡ የተመረጡ ተፋሰሶች ዝርዝር*

| ተ/ቁ | ክልል | ዞን | ወረዳ | ተፋሰስ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አማራ | ምስራቅ ጎጃም | መቻከል | ቢቡኝ |
| | | ምዕራብ ጎጃም | ቡሬ ዙሪያ | ቻንታሊ |
| 2 | ኦሮሚያ | ምስራቅ ሐረርጌ | ሀራማያ | ሀሮማያ |
| | | ምዕራብ ሸዋ | ኤጄሬ | በርጋ |
| | | ምዕራብ ሸዋ | ወንጪ | ወንጪ |
| 3 | ሲዳማ | ዞን 1 | አርቤጎና | ገላና |
| 4 | ደቡብ | ሀዲያ | ሶሮ | ልንታሳ |
| | | ስልጤ | ምዕራብ አዘርነት | ጡጃ |
| | | ጉራጌ | ጉመር | ፉስር |
| 5 | አፋር | | | በምክክር በቀጣይ የሚመረጥ |

## 8. የውጤት አመልካቾች

ሠንጠረዥ 3፡ በተፋሰሱ የሚተገበሩ የቅንጅታዊ ሥራ ተግባራትና የውጤት አመልካቾች

| የትኩረት መስኮች | ዓበይት ተግባራት | የአጭር ጊዜ የውጤት አመልካቾች | የመካከለኛና ረጅም ጊዜ የውጤት አመልካቾች | ደጋፊ ፕሮጀክቶች |
|---|---|---|---|---|
| የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም | • በመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መሰረት ተፋሰስ ማልማት | • በመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መሰረት የለማ ተፋሰስ በመቶኛ | • የጨመረ የዕፅዋት ሽፋንና ስብጥር በመቶኛ<br>• የቀነሰ የአፈር ክለት በመቶኛ<br>• የተሸሻለ የአፈር ውሃ የመያዝ አቅም በመቶኛ፣<br>• የጨመረ የከርሰ ምድር ውሃ ይዘት በመቶኛ<br>• የተገለለ ሙቀት አማቂ ጋዝ (ሜ/ቶን)<br>• የቀነሰ ልቅ ግጦች በመቶኛ<br>• ያደገ የግብርና ምርት በመቶኛ<br>• ያደገ ገቢ በመቶኛ፣<br>• የተሸሻለ ምግብና ሥርዓተ-ምግብ በመቶኛ<br>• ያደገ አየር ንብረት ለውጥ የመላመድና የመቋቋም አቅም በመቶኛ | • CALM<br>• RLLP/SLM<br>• PACT<br>• PSNP/PW |
| | • ስነ-ህይወታዊ እና ስነ-አካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎችን መሥራት | • ስነ-ህይወታዊ እና ስነ-አካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች የተተገበሩበት መሬት በሄ/ር | | |
| | • ጥገና ዕድሳትና ደረጃ የማሳደግ ሥራዎች | • ጥገና ዕድሳትና ደረጃ የማሳደግ ሥራ የተሠራላቸው ስትራክተሮች በኪ/ሜር | | |
| | • የአየር ንብረት ለውጥ የሚቋቋም ግብርና | • የአየር ንብረት ለውጥ የሚቋቋም ግብርና ቴክኖሎጂዎች የተሸፈነ የመሬት ስፋት በሄ/ር | | |
| | • የተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማህበረትን ማቋቋም እና የተቋቋሙትን ማጠናከር | • የተቋቋመና የተጠናከረ የተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማህበረት ብዛት በቁጥር | | |
| | • የማህበረሰብ ደን ልማት | • የለማ የማህበረሰብ ደን ሽፋን በሄ/ር | | |
| | • ጥምር ደን እርሻ ልማት | • የለማ ጥምር ደን እርሻ ልማት ስፋት በሄ/ር | | |
| | • የተጎዳ መሬትን ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ነፃ ማድረግ | • ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ነፃ የሆነ የተጎዳ መሬት በሄ/ር | | |
| | • የጓሮ የመኖ ልማትና አስተዳደርን ማዳበር፣ | • የለማ ጓሮ መኖ በሄ/ር<br>• እንስሳትና አሥሮ መመገብን ተግባራዊ ያደረጉ አርሶ አደሮች በመቶኛ | | |
| | • የለሙ ተፋሰሶች ለብሄራዊ የካርቦን ድርሻ (NDC) ያላቸውን አስተዋጽኦ መለካት፣ | • ልኬት የተካሄደባቸው ተፋሰሶች ብዛት በቁጥር | | |

| የትኩረት መስኮች | ዓበይት ተግባራት | የአጭር ጊዜ የውጤት አመልካቾች | የመካከለኛና ረጅም ጊዜ የውጤት አመልካቾች | ደጋፊ ፕሮጀክቶች |
|---|---|---|---|---|
| | • ከተፋሰሱ የተገለለ ሙቀት አማቂ ጋዝን መለካት፣ | • ልኬት የተካሄደባቸው ተፋሰሶች ብዛት በቁጥር | | |
| የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም | • ተሳትፎአዊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ማዘጋጀትና መተግበር<br>• ግጦሽ<br>• የማህበረሰብ ደን<br>• የመኖሪያ<br>• የሰብል (ቋሚ፣ ዓመታዊ) | • የተዘጋጀና የተተገበረ ተሳትፎአዊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በቁ/ር | | • CALM<br>• LAGO<br>• RAILA |
| | • 2ኛ ደረጃ የመሬት ልኬት፣ ምዝገባና ማረጋገጫ | • 2ኛ ደረጃ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ያገኙ አ/አደሮች ብዛት በቁ/ር | | |
| | • ከመሬት የመጠቀም መብት ጋር የተያያዘ ብድር እንዲያገኙ ማድረግ | • ብድር ያገኙ አርሶ አደሮች ብዛት በቁ/ር | | |
| | • የመሬት የማምረት አቅም ምደባን መተግበር | • የመሬት የማምረት አቅም ምደባ የተተገበረባቸው ተፋሰሶች ብዛት በቁ/ር | | |
| | • ከመሬት የመጠቀም መብት ጋር የተያያዘ ብድር | • | | |
| የአነስተኛ ይዞታ መስኖ ልማት | • ውሃ ማሰባሰብ | • | ከዝናብ ጥገኝነት የመላቀቅ ምጣኔ በመቶኛ | • SHIDP<br>• PACT<br>• DR-DIP |
| | • የቤተሰብ መስኖ (ፓምፕ፣ የቅርብ ከርሰምድር ውሃ፣ ገንዳ እና የመሳሰሉት) | • በቤተሰብ መስኖ የለማ መሬት በሄ/ር | | |
| | • የማህበረሰብ መስኖ ልማት (ወንዝ/ምንጭ መጥለፍ፣ ኩሬ፣የከርሰምድር ውሃ፣ ፓምፕ) | • በማህበረሰብ መስኖ የለማ መሬት በሄ/ር | | |
| | • የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር ማቋቋም እና ማጠናከር | • የተቋቋመና የተጠናከረ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ማህበር ብዛት በሄ/ር | | |
| | • የመስኖ ውኃ አጠቃቀምን ውጤታማነት የሚያጎለብቱ የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን ማላመድ | • የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን የተገበሩ አ/አደሮች ብዛት | | |

| የትኩረት መስኮች | ዓበይት ተግባራት | የአጭር ጊዜ የውጤት አመልካቾች | የመካከለኛና ረጅም ጊዜ የውጤት አመልካቾች | ደጋፊ ፕሮጀክቶች |
|---|---|---|---|---|
| | • የተፋሰሱን የመስኖ ዕምቅ አቅም ማጥናት | • የተፋሰሱ የመስኖ ዕምቅ አቅም የጥናት ዶክመንት ብዛት | | |
| የአፈር ለምነትና ጤንነት | • የአፈር ዓይነትና ለምነት ካርታ ማዘጋጀት | • የተዘጋጀ የአፈር ዓይነትና ለምነት ካርታ | • የተሸሻለ የአፈር ጥልቀት መሻሻል በሳ.ሜ፣<br>• የተሸሻለ የአፈር ካርቦናዊ ቁስ ይዘት በመቶኛ፣<br>• የቀነሰ የአፈር ሆምጣጤነት በመቶኛ<br>• የቀነሰ የአፈር ጨዋማነት በመቶኛ<br>• የጨመረ የአፈር ንጥረ ነገር ይዘት በመቶኛ | • SLM<br>• CALM<br>• ISFM<br>• PACT |
| | • ኮምፖስት/ቬርሚ ኮምፖስት ማልማት | • በኮምፖስት/ቬርሚ ኮምፖስት የለማ ማሳ በሄ/ር | | |
| | • አሲዳማ አፈር ማከም | • በግብረና ኖራና በአማራጭ ቴክኖሎጂዎች የታከመ አሲዳማ አፈር በሄ/ር | | |
| | • የኮትቻ አፈር ልማት | • በዘመናዊ አሠራር በማንጣፈፍ የለማ ኮትቻማ አፈር ስፋት በሄ/ር | | |
| | • የጨዋማ አፈር ልማት | • አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የለማ ጨዋማ አፈር ስፋት በሄ/ር | | |
| | • ጥብቅ እርሻ ማስፋፋት | • ጥብቅ እርሻ ተግባራዊ የተደረገበት ማሳ በሄ/ር | | |
| | • ህየው ማዳበሪያ አጠቃቀም ማሻሻል | • በህያው ማዳበሪያ የለማ ማሳ ስፋት በሄ/ር | | |
| | • የአፈር እና ሰብል ዓይነትን መሰረት ያደረገ የማዳበሪያ አጠቃቀም ምክረ ሃሳብ እንዲኖር ማድረግ፣ | • የአፈር እና ሰብል ዓይነትን መሰረት ያደረገ የማዳበሪያ አጠቃቀም ተግባራዊ የተደረገበት ማሳ ስፋት በሄ/ር | | |

# 9. የአቅም ግንባታ ሥራ

የቅንጅታዊ አሠራሩን የሙከራ ተግባር ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥራዎች በየደረጃው ሊሠሩ ይገባል፡፡

## 9.1. የሰው ኃይል አቅም ግንባታ

ከፌዴራል ጀምሮ እስከ ተፋሰስ ድረስ ያሉ አስፈፃሚዎች በቅንጅታዊ አሠራር አመራርና አፈፃፀም ዙሪያ አመለካከት፣ ክህሎትና ዕውቀት የሚያሳድጉ ሥልጠናዎች በተደራጀ ሁኔታ እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም በቅንጅታዊ አሠራሩ የሚፈፀሙ ተግባራት በሚፈልጉት አዳዲስና በምርምር የተገኙ ቴክኖሎጂዎችና አሠራሮች ላይ ሥልጠና እንዲወስዱ ይደረጋል፡፡ የተጠቃሚውን ማህበረሰብ ግንዛቤ፣ ዕውቀትና ክህሎት የሚያሳድጉ ሥልጠናዎች በዳሰሳ ጥናት ውጤት ላይ ተመሥርተው እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

## 9.2. የቁሳቁስ አቅም

በየደረጃው የቅንጅታዊ አሠራሩን ውጤታማ ለማድረግ የሚያግዙ ቴክኖሎጂዎች እና ማቴሪያሎች በተጠናና በተቀናጀ ሁኔታ ሙከራ ለሚደረግባቸው ወረዳዎች እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡

# 10. የባለድርሻ አካላት ልየታና ሚና

ለዚህ ቅንጅታዊ ሥራ በርካታ አጋር አካላትን የሚጠይቅ ሲሆን የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

ሠንጠረዥ 4፡ የባለድርሻ አካላት ሚና

| ተ/ቁ | ባለድርሻ አካላት | የባለድርሻ አካለት ዝርዝር | ተግባርና ኃላፊነት |
|---|---|---|---|
| 1 | ሚኒሰቴር መ/ቤቶች | • ግብርና፣ ውኃና ኢነርጂ፣ ፕላንና ልማት፣ መስኖና ቆላማ፣ ገንዘብ፣ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ | • አንድ ወጥ የሆነ አሳታፊ ሀገራዊ መድረክ እና የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት<br>• አስፈላጊ ሀብት ማፈላለግና መመደብ |
| 2 | የግብርና ሚኒስቴር ዘርፎችና ተጠሪ ተቋማት | • ተፈጥሮ ሀብት፣ እርሻና ሆረቲካለቸር፣ እንስሳት ሀብት፣ የእርሻ ኢንቨስትመንትና ግብዓት ዘርፎች<br>• ደን ልማት፣ ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ብዝሐ-ሕይወት ኢንስቲትዩት | • አመታዊ የቅንጅታዊ አሰራር ዕቅድ መንደፍና መተግበር፣<br>• የሥራ ክፍሎችንና ፕሮግራሞችን/ፕሮጀክቶችን መምራት፣<br>• በየዘርፉ ያሉ ቅንጅታዊ መድረኮችን እና የሥራ ክፍሎችን ማናበብ፤<br>• ቅንጅታዊ አሰራሩን የሚመራ አሃድ መሰየም፣<br>• ቅንጅታዊ አሰራሩ በክልል፣ በዞን እና በወረዳ ተፈፃሚ እንዲሆን አመራር መስጠትና ድጋፍ ማድረግ፣ |
| 3 | በተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ ውስጥ ያሉ የሥራ ክፍሎች | • የተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም፣ የአፈር ሀብት ልማትና የአነስተኛ ይዞታ መስኖ ልማት | • የቅንጅታዊ አሰራር ማነቆዎችን በመለየት ማቅረብ፣<br>• የቴክኒክ ኮሚቴ አባላትን መመደብ፣ |
| 4 | የግብርና ሚኒስቴር ዘርፈ-ብዙ የሥራ ክፍሎች | • የግብርና ሥራ ዕድል ፈጠራና ከተማ ግብርና ልማት፣ ሥርዓተ-ፆታ፣ ምግብና ሥርዓተ-ምግብ፣ ምግብ ዋስትና፣ የአየር ንብረት ለውጥ | • የቅንጅታዊ አሰራር ማነቆዎችን በመለየት ማቅረብ፣<br>• የቴክኒክ ኮሚቴ አባላትን እንደአስፈላጊነቱ መመደብ፣ |
| 5 | የኅብረት ሥራ ማኅበራት | • የማኅበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች የኅብረት ሥራ ማኅበራት<br>• የመስኖ ውኃ ተጠቃሚ ማኅበራት | • ከማህበረሰቡ የሚጠበቀውን ድርሻ ማሰባሰብ እና መምራት፣<br>• የሚገኘውን ሀብትና ውጤት ለማህበረሰቡ በፍትሃዊነት ተደራሽ ማድረግ፣ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | • መሰረታዊ የህብረት ሥራ ማህበራት | • የግብዓት አቅርቦት እና ገበያ ትስስር መፍጠር፣ |
| 6 | የልማት አጋሮችና የፋይናንስ ተቋማት | • የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ የሚያደርጉ ተቋማት | • ከመንግስት በሚቀርበው ጥያቄ መሰረት የፋይናንስ እና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ማድረግ፣<br>• ለአባላት እና ለማህበራት የብድር አገልግሎት ማቅረብ፣ |
| 7 | በተፋሰስ ውስጥ ያሉ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች | • በተፋሰስ ውስጥ በሚደረግ የዳሠሳ ጥናት የሚለዩ | • ለቅንጅታዊ አሰራሩ ስኬት መሰረት መፍጠር |

# 11. ዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ

## 11.1. የዕቅድ ዝግጅት

የተመረጡ ተፋሰሶችን የልማት ዕቅድ መነሻ በማድረግ ሁሉም የተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ የሥራ ክፍሎች፣ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች እና በዚህ ሠነድ የተለዩ ባለድርሻና አጋር አካላት በቅንጅታዊ ዕቅድ ዝግጅት መርኅ መሠረት በጋራ የሚያቅዱ ይሆናል፡፡ የዕቅዱ መነሻ በናሙናነት የተመረጡ የማህበረሰብ ተፋሰሶች ያላቸውን ጸጋ መሠረት ያደረገ ሆኖ ቅድሚያ መፈታት ያለባቸውን የተለዩ ችግሮች ላይ በማተኮር ከታች ወደ ላይ የዕቅድ ዝግጅት ሂደትን የሚከተል ይሆናል፡፡ ለሙከራ ጊዜ ተፋሰሶች የሦስት ዓመታት ስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅድ የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡ በተመሣሣይ ለማስፋት ጊዜ በሚመረጡ ተፋሰሶች የአምስት ዓመታት ስትራቴጂክና ዓመታዊ ዕቅድ ይዘጋጃል፡፡

## 11.2. የድጋፍ፣ የክትትልና የሪፖርት ሥርዓት

የሙከራ ጊዜ የቅንጅታዊ አሠራር ትግበራ በተፈጥሮ ሀብት ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ የበላይ አመራር ሰጭነት የሚመራ ሲሆን በስሩም በዘርፉ ያሉት የየሥራ ክፍል ኃላፊዎችን እና የፕሮጀክት/ፕሮግራም አስተባባሪዎችን እንዲሁም የቅንጅታዊ አሰራር አሀድ አስተባባሪን ባካተተ መልኩ ይሆናል፡፡ ለዚህ ስኬት እንዲያግዝ የዘርፉ ማኔጅመንት በሚያደርገው ወቅታዊ ስብሰባ ቅንጅታዊ አሠራር አንድ አጀንዳ ሆኖ ይቀርባል፣ ይገመገማል፣ አቅጣጫ ይሠጥበታል፡፡

በቅንጅት የሚሠሩ የተፋሰስ ልማት ተግባራትን አፈጻጸም ድጋፍና ክትትል የሚካሄደው በቅንጅታዊ አሰራር አሀድ አስተባባሪ እየተመራ ከየስራ ክፍሎቹና ከፕሮጀክት/ፕሮግራም ከአሀዱ ጋር እንዲሰሩ በሚመደቡ ባለሙያዎች እንዲሁም በክልልና ወረዳ ደረጃ በሚሰየሙ ተጠሪ ባለሙያዎች (Focal persons) ክትትልና ድጋፍ የሚፈጸም ይሆናል፡፡ በዕቅዱ መሠረት የተከናወኑ ተግባራትን በየሩብ ዓመቱ የግምገማ መድረክ በማዘጋጀት የሚካሄድ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ ጊዜውን ሳይጠብቅ በተመረጡ ተፋሰሶች ላይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን መሠረት በማድረግ ሊገመገም ይችላል፡፡

የክትትልና ድጋፍ ሥራው በዕቅድ ክንውን ላይ በማተኮር በመጀመሪያ ድጋፍ የሚሰጥባቸውን ወቅታዊ ስራዎችን የመለየት፣ የመከታተያ ነጥቦችን በቼክ ሊስት የማዘጋጀት፣ ተጨባጭ መሬት ላይ ያሉ

ጠንካራ ጎኖችን እና ክፍተቶችን የመለየት ሥራዎችን በመስራት ከክልል እስከ የማህበረሰብ የተፋሰስ ኮሚቴዎች ድረስ ግብረ - መልስ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም የመስክ መልስ የክትትልና ድጋፍ ሪፖርት በማዘጋጀት ለተቋቋመው አሃድ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡ የሪፖርት ቅብብሎሹ የቅንጅታዊ አሰራር ማስተባበሪያ አሀድ በሚያዘጋጀው ወጥ በሆነ የሪፖርት ፎርማት መሠረት ከማህበረሰብ አቀፍ የተፋሰስ ህብረት ሥራ ማህበራት ጀምሮ በተዋረድ እስከ ዘርፍ ማኔጅመንት ድረስ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

## 11.3. የምርምርና ሥርፀት መድረክ

በውጤት አመልካቾች ሥር ከተጠቀሱት ዋና ዋና ተግባራት መካከል በምርምር የሚፈቱ ክፍተቶችን ለይቶ አሳታፊ የሆነ የምርምር ሥርዓት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በዚህ የተገኘውን ውጤት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ዓመታዊ የምርምርና ሥርፀት መድረክ በማዘጋጀት ወይም ያሉትን ሌሎች መድረኮች በመጠቀም ለፈፃሚና ለተጠቃሚ አካላት የማስተዋወቅ ሥራ ይሠራል፡፡

## 11.4. ምርጥ ተሞክሮ የማስፋት ሥራ

የቅንጅታዊ ሥራው ዋና ዓላማ ሞዴል ተፋሰሶችን በመፍጠር የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን ወደ ሌሎች ተፋሰሶች ማስፋት በመሆኑ የሞዴል ተፋሰሶች የመመዘኛ መሥፈርት የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡ በሞዴል መመዘኛ መስፈርቱ መሠረት ብቁ ከሆኑ ተፋሰሶች ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ወደ ሌሎች ተፋሰሶች የማስፋት ሥራ ይሠራል፡፡

# 12. ስጋቶች እና የመፍትሔ ርምጃዎች

ሠንጠረዥ 5፡ ስጋቶችና የመፍትሔ ርምጃዎች

| ታሳቢዎችና ሥጋቶች | የመፍትሔ ርምጃዎች |
|---|---|
| በየደረጃው የአመራር መለዋወጥ | አዲስ ወደ አመራርነት የሚመጡ አካላትን ግንዛቤ የሚያሳድግ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት |
| በመስኩ የሠለጠነ የሰው ሀብት ዕጥረትና ፍልሰት፣ | አዲስ የሚቀላቀሉ ባለሙያዎችን ዕውቀትና ክህሎት የሚሳድጉ የአቅም ግንባታ ሥዎችን መሥራት |
| የፈፃሚ፣ አስፈፃሚና ባለድርሻ አካላት ቁርጠኝነትና ትኩረት ማነስ | ተከታታይ ግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን ማዘጋጀት |
| የድጋፍ ሰጭ አካላት ፈቃደኝነት ተለዋዋጭነትና | የሀብት ብክነትን በመቀነስ በአግባቡ መጠቀም፤ አገራዊ የውስጥ አቅም በዘላቂነት ለማጎልበት የሚያስችሉ አማራጮችን መቀየስ፤ |
| ድርቅና የአየር ንብረት ለውጥ | የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ የመቋቋም አቅም ማሳደግ |
| የፀጥታ ችግር | ከሚመለከታቸው ጋር የግጭት ማስወገጃ መንገዶች ዙሪያ በቅንጅት መስራት |
| ከውጭ የሚገቡ ግብዓቶች አቅርቦት እጥረት | በሀገራዊ ምርት እንዲተኩ ከሚመለከታቸው ጋር በቅርበት መስራት |

# 13. የሚያስፈልግ በጀት

## 13.1. የሙከራ ሥራ በጀት

ለቅንጅታዊ አሠራር ለሙከራ ትግበራ በሚመረጡ ተፋሰሶች ውስጥ በትግበራ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞችን፣ በመደበኛ የሚመደቡ በጀቶችን እና የማህበረሰቡን አስተዋጽኦ በማስተባበር አንድ ወጥ የቅንጅታዊ አሠራር ዕቅድ በማዘጋጀት በወረዳው አስተዳደር እየተመራ የሚተገበር ሲሆን ለሙከራ ትግበራ ሥራው ተብሎ የሚመደብ ራሱን የቻለ በጀት አይኖርም፡፡ ይሁን እንጅ በሙከራ ትግበራው ተፋሰሶች ውስጥ ያሉትን የልማት ክፍተቶችን ለመሙላት ባልተቻለበት ወቅት እንደየሁኔታው ተጨማሪ በጀት የማፈላለግ ሥራ የሚሠራ ይሆናል፡፡ በመሆኑም የቅንጅታዊ አሠራር በጀት የሚዘጋጅላቸው በውጤት አመላካቾች ሥር የተዘረዘሩ ተግባራትን መነሻ በማድረግ ይሆናል፡፡

## 13.2. የማስፋት ዘመን በጀት

- በሙከራ ትግበራ ወቅት የተገኘውን መልካም ውጤትና ልምድ በማስፋት ትግበራው በሚሰፋባቸው ተፋሰሶች ውስጥ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን/ፕሮግራሞችን፣ በመደበኛ የሚመደቡ በጀቶችን እና የማህበረሰቡን አስተዋጽኦ በማስተባበር የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡
- የሚቀረጹ አዳዲስ ፕሮጀክቶች/ፕሮግራሞች የቅንጅታዊ አሰራሮችን መሰረት በማድረግ እንዲቃኙ ይደረጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለቅንጅታዊ አሰራሩን የልማት ክፍተቶች ለመሸፈን ተብሎ የሚቀረጹ አዳዲስ ፕሮጀክቶች እንዳስፈላጊነቱ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡
- በሙከራ ትግበራ ወቅት የተገኙ ልምዶችን መሠረት በማድረግ በየተፋሰሱ የሚተገበሩ ነባር ፕሮጀክቶች የቅንጅታዊ አሰራርን መርኅን እንዲከተሉ ይደረጋል፡፡

*ሠንጠረዥ 6፡ የቅንጅታዊ ሥራዎች የሦስት ዓመት የሙከራ ጊዜ ሠሌዳ*

| ተ/ቁ | የስራ ዝርዝር | ፈጻሚ | የጊዜ ሰሌዳ |
|---|---|---|---|
| 1 | የቅንጅታዊ አሠራር የማዕቀፍ ሰነድ ዝግጅት ለዘርፍ አመራር ማቅረብ፥ ማስተቸትና በማኔጅመንት አካላት ማጸደቅ | ተፈጥሮ ሃብት ልማት ዘርፍ | ከጥር 5-15/2015 ዓ/ም |
| 2 | በቅንጅታዊ ሰነዱ ላይ ለሚመለከታቸዉ የፌደራል እና ለክልል ባለድርሻ አካለት የጋራ ግንዛቤ ለመፈጠር አወደጥናት ማካሄድ | የቅንጅታዊ ስራዎች ቴክኒክ ቡድን | ሚያዝያ 16-20/2015ዓ/ም |
| 3 | ለቅንጅታዊ የሙከራ ስራዎች ተፋሰሶችን መለየትና የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ (በታፋሰሱ ዉስጥ የተሰሩ እና ቀሪ ስራዎችን መለየት፥ አጋር አካላትን መለየት) | የቅንጅታዊ ስራዎች ቴክኒክ ቡድን | መጋቢት 7-30/2015 ዓ/ም |
| 4 | ለሙከራ ትግበራ በተመረጡ ተፋሰሶች ላይ ያለዉን እቅድ ለቅንጅታዊ አሰራሩ በሚያመች መልኩ መከለስና የሶስት ዓመት እና ዓመታዊ ዕቅድ ማዘጋጀት | የዕቅድ ዝግጅት ኮሚቴ | ሚያዝያ 1-15/2015ዓ/ም |
| 6 | በቅንጅታዊ ሰነዱ ላይ ለሚመለከተቸዉ የዞን፥ የወረዳና የተፋሰስ ባለድርሻ አካለት የጋራ ግንዛቤ ለመፍጠር አወደጥናት ማካሄድ | የቅንጅታዊ ስራዎች ቴክኒክ ቡድን | ሚያዝያ 21-25/2015ዓ/ም |
| 7 | የተከለሰዉን እቅድ ለፈጻሚ አካላትና ለማህበረሰቡ ማሰተዋወቅ | በየደረጃዉ ያሉ ቴክኒክ ቡድን አባላት | ከግንቦት 1-5/2015 ዓ/ም |
| 8 | የቅንጅታዊ ስራዎች ዕቅድ ትግበራ ማስጀመር | በየደረጃዉ ያሉ ፈጻሚ አካላት | ግንቦት 10/2015 ዓ/ም |
| 9 | የክትትልና ግምገማ ስራዎችን ማካሄድ | በየደረጃዉ ያሉ የቴክኒክ ኮሚቴዎችና የፌደራል ማስተባበሪያ አሃድ | ሰኔ 1/2015 ዓ/ም ጀምሮ |

| ተ/ቁ | የስራ ዝርዝር | ፈጻሚ | የጊዜ ሰሌዳ |
|---|---|---|---|
| 10 | የቅንጅታዊ ስራዎችን የመካከለኛ ጊዜ አፈጻጸም መገምገም | በየደረጃዉ ያሉ የማኔጅምንት አካላት፣ የፌደራል ማስተባበሪያ አሃድ እና የቴክኒክ ኮሚቴዎች | ጥር 2017 ዓ/ም |
| 11 | ምርጥ ተሞክሮዎችን መለየትና መቀመር | የፌደራል ማስተባበሪያ አሃድ እና የቴክኒክ ኮሚቴዎች | ከ የካቲት 1/2017 እስከ የካቲት 30/2018 ዓ/ም |
| 12 | የቅንጅታዊ ስራዎች የሙከራ ትግበራ አፈጻጸም ግምገማ ማካሄድና የቀጣይ አቅጣጫ ማስቀመጥ | በየደረጃዉ ያሉ የማኔጅምንት አካላት፣ የፌደራል ማስተባበሪያ አሃድ እና የቴክኒክ ኮሚቴዎች | ግንቦት 2018 ዓ/ም |
| 13 | የአምስት ዓመት የቅንጅታዊ ስራዎች ትግበራ ዕቅድ ማዘጋጀት | የፌደራል ማስተባበሪያ አሃድ እና የቴክኒክ ኮሚቴዎች | ከጥር 1/2018 እስከ ሰኔ 30/2018 ዓ/ም |

# ዋቢ/ማጣቀሻ


- Amare etal, (2020) Community-based Participatory Watershed and Rangeland Development: A Guideline, Part 1. Ministry of Agriculture, Ethiopia, Addis Ababa.
- ግብርና ሚኒስቴር (2012)የግብርና ዘርፍ የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ አዲስ አበባ
- የግብርና ሚኒስቴር (2013) ረቂቅ የተሻሻለ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ አዲስ አበባ